አባ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣
ሊቀ ጳጳስ ዘአኵስም፣
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣

ABBA MATTHIAS I
Patriarch of Ethiopia, Archbishop of Axum.
Echegue of the See of St. Tekle Haimanot

ቁጥር ፀ/ጀ/179/338/2008
Ref. No

ቀን 16/5/2008 ዓ.ም
Date

ለቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ

ለሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ

አዲስ አበባ

ለቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ

መቐሌ

## ጉዳዩ:- መመሪያ ማስተላለፍን ይመለከታል፤

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጌታችን ትምህርት ተመሥርቶ በቅዱሳን ሐዋርያትና ከዚያም በየጊዜው በተነሡ አበው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የተደነገገ ቀኖና ያላት ሐዋርያዊትና ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ናት ።

ቤተ ክርስቲያናችን ለሁለት ሺሕ ዓመታት ያህል በዚህ ቀኖና እየተመራች ሃይማኖቷን፣ ትውፊቷንና ባህሏን ጠብቃ፣ አንድነቷን አጽንታ ኖራለች ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና ሐዋርያትን መሠረት አድርጋ የምትመራ ቤተ ክርስቲያን እንደመሆኗ መጠን ዛሬም ኦርቶዶክሳዊውን የአመራር ሥርዓት ማለትም በቅዱስ ሲኖዶስ የሚመራ ቀኖናዊ ሥርዓትን ተከትላ መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥራዋን ታከናውናለች ።

በዚህ ቀኖና መሠረት የቤተ ክርስቲያናችን መሪና ውሳኔ ሰጭ የመንበረ ሐዋርያት ወራሽ የሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ እንጂ የተለያየ ስምና አደረጃጀት ያላቸው ማኅበራት አይደሉም። እንደዚህ ያለ ሥርዓት የኦርቶዶክሳውያን አለመሆኑም በግልጽ ሊሰመርበት ይገባል ።

በተለይም ማኅበረ ቅዱሳን የተባለ ማኅበር የቅዱስ ሲኖዶስን ሥልጣን በመጋፋትና ቤተ ክርስቲያንን በማተራመስ ቀኖና የለሽ ሥርዓት ሲከተል ይስተዋላል ።

ማኅበረ ቅዱሳን ጥቅሙና ጉዳቱ በሚገባ ሳይጠና ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን አንጻር የሚያስከትለው የሃይማኖትና የሥርዓት ተፋልሶ ሳይፈተሽ በአንድ ወቅት ራሱ አርቆና አዘጋጅቶ ባቀረበው ደምብ



☎ 251-111-111989, 251-111-550577, 251-111-... 251-111-551013
Fax:- 251-111-552211
☒ 1283 አዲስ አበባ Addis Ababa
E-mail: abbamatthiaspatriarch@yahoo.com
abagerima@yahoo.com

አባ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣

ABBA MATTHIAS I
Patriarch of Ethiopia, Archbishop of Axum,
Echegue of the See of St. Tekle Haimanot

ቁጥር
Ref. No

ቀን ዓ.ም
Date

በቅዱስ ሲኖዶስ የተፈቀደልኝ ሕጋዊ ማኅበር ነኝ በማለት በቤተ ክርስቲያን መዋቅር ልክ ከላይ እስከታች መዋቅር ዘርግቶና ከቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ውጭ የሆነ ሌላ ቤተ ክርስቲያን አከል ተቅዋም መሥርቶ ታሪክ ይቅር የማይለው ጥፋት እየፈጸመ ይገኛል ።

በዚህ አድራጎቱ ከኦርቶዶክስ ቀኖና ውጭ በመዋቅር ያልታቀፉ ስፍር ቁጥር የሌላቸውና የተበታተኑ ማኅበራት እንዲፈጠሩና ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ውጭ በየመንደሩና በየአዳራሹ እንዲሰበሰቡ በማድረግ ኦርቶዶክሳዊ ያልሆነ ባህልን እንዲለማመዱ፣ እንደዚሁም ከኦርቶዶክስ ቀኖና እንዲያፈነግጡ መጥፎ በር በመክፈት የነገይቱ ቤተ ክርስቲያን ሰው አልባ የሚያደርግ ሁኔታ ፈጥሯል ።

ማኅበሩ ከፈጸማቸው አበይት ጥፋቶች መካከል ጥቂቶቹን ለመጥቀስ፤

ሀ/ በሌለው ሥልጣን የጾም አዋጅን እስከማወጅ መድረሱን፤

ለ/ በቤተ ክርስቲያኗ ገዳማትና የአብነት ትምህርት ቤቶች ስም በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ያለ ካርኒ ከፍተኛ ገንዘብ በመሰብሰብ ቤተ ክርስቲያን በማታውቀው አሠራር ለድብቅ ዓላማው ማስፈጸሚያ ማዋሉን፤

ሐ/ ከቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን አመራር አለመቀበሉና አባቶችን መዳፈሩን፤

መ/ የቤተ ክርስቲያን አመራር አካላት በመከፋፈል በሐሰት የፕሮፖጋንዳ ቅስቀሳ ተፅዕኖ በመፍጠርና በማታለል የቤተ ክርስቲያንን አንድነት መፈታተኑንና በምትኩ ደግሞ የራሱን ማኅበር ብቸኛ ጠንካራ አስመስሎ በማሳየት ሕዝቡን ግራ ማጋባቱ፤

ሠ/ ከቤተ ክርስቲያን ሳይጠይቅና ሳይፈቀድለት በቤተ ክርስቲያን መዋቅሮች ጣልቃ እየገባ የአብነት መምህራንን፣ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶችንና ገዳማውያንን በመሰብሰብ ለድብቅ ዓላማው መሣሪያ እንዲሆኑ በገንዘብም ጭምር ማታለልን ሥራዬ ብሎ መቀጠሉን፤

2

☎ 251-111-..1198, 251-111-550577, 251-111-..5747, 251-111-5516.. Fax:- 251-111-552211
1283 አዲስ አበባ Addis Ababa
E-mail: abamatthiaspatriarch@yahoo.com
abagerima@yahoo.com

አባ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣

ABBA MATTHIAS I
Patriarch of Ethiopia, Archbishop of Axum,
Echegue of the See of St. Tekle Haimanot

ቁጥር
Ref. No

ቀን
Date

ረ/ በሃይማኖታዊ መርህ ሳይሆን በሥውር ኮሚቴ የሚመራና በረቀቀ የስለላ ሥራ የተሠማራ መሆኑን በራሱ አባል የተጋለጠ ከመሆኑ አንጻር ይቃወሙኛል በሚል ስጋት የሊቃውንትንና የካህናትን ስም በማጥፋት ያለዕረፍት እየሠራ መሆኑን፤

ሰ/ በቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ ሥራዎች ጣልቃ በመግባት ይቃወመኛል ብሎ የሚጠረጥረውን በማሳደድ፣ ደጋፊዬ ነው የሚለውን በመደበቅ ኢ-ክርስቲያናዊ ተግባር መፈጸም የዘወትር ተግባር ማድረጉን፤

ሸ/ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት በተለይም በውጭ ሀገር የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በእርሱ አመራርና ትእዛዝ ስር ብቻ ሆነው እንዲሠሩ ተጽዕኖ መፍጠር፣ አለያም እርስ በርስ እየከፋፈለ ማተራመስ ከዚያም አልፎ በማኅበሩ ስም ቤተ ክርስቲያንን እየተከለ የማኅበር ቤተ ክርስቲያንን መፍጠሩን፤

ቀ/ ተጠያቂነትንና ግልጽነትን የሚያረጋግጥ ደንብ እንዲኖረው ታስቦ በቅዱስ ሲኖዶስ የተወሰነውን የደንብ ማርቀቅ ሥራ ሆን ብሎ በማሰናከል ያለ ደንብ እየሠራ መሆኑን፤

በ/ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያልታቀፈ የማኅበር አደረጃጀት ፈጥሮ ለሌሎች መጥፎ አርአያና ምሳሌ በመሆኑ ወጣቱ ትውልድ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን በተዋቀረ የሰንበት ት/ቤት ተቀዋም ተደራጅቶ ቤተ ክርስቲያንን እንዳያገለግል በየመንደሩ እየተደራጀና በየአዳራሹ እየተሰበሰበ ኢ-ኦርቶዶክሳዊ የሆነና የተበታተነ አደረጃጀት እንዲፈጠር፣ የነገዋ ቤተ ክርስቲያንም ሰው አልባ ወይም የተበታተነች አቅመ ደካማ ቤተ ክርስቲያን እንድትሆን በማድረግ እጅግ በጣም ጎጂ ባህልን ማለማመዱን፤



☎ 251-111-... 251-111-550577 Fax:- 251-111-552211 E-mail: abamatthiaspatriarch@yahoo.com
251-111-... 251-111-... 1283 አዲስ አበባ Addis Ababa abagerima@yahoo.com

አባ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣
ሊቀ ጳጳስ ዘአኲስም፣
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣

ABBA MATTHIAS I
Patriarch of Ethiopia, Archbishop of Axum,
Echegue of the See of St. Tekle Haimanot

ቁጥር
Ref. No

ቀን ዓ.ም
Date

ተ/ ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጭ ያለ በቂ መንፈሳዊ ትምህርትና ስሙ ተለይቶ ባልታወቀ ቤተ ክርስቲያን ለአባላቱ የጅምላ ክህነት እያሰጠ ክህነትን ለድብቅ ዓላማው ማስፈጸሚያ መጠቀሙን፤

ቸ/ ሀብታሞችን ለይቶ በአባልነት በመቀበል ለቤተ ክርስቲያን የሚገባውን አስተዋፅኦ ለራሱ ማኅበር ማስገባቱን መንግሥትም ሆነ ቤተ ክርስቲያን የማያውቁትና የማይቆጣጠሩት ሀብት ማድለቡን፣ ቤተ ክርስቲያን እንዳትቆጣጠረውም በእምቢተኝነት መጽናቱን በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው ።

በአጠቃላይ ማኅበረ ቅዱሳን ቢቻል የቤተ ክርስቲያንን መዋቅር ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር በማዋል ድብቅ ዓላማውን ለማሳካት አልያም የራሱ የሆነ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ፈጥሮ በተራዘመ የማተራመስና የመከፋፈል ስልት ያሰበውን ሥውር ዓላማ ለመፈጸም እየተጣደፈ መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው ።

የዚህም ዋና ማሳያ የሚሆነን የቤተ ክርስቲናችን ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን በመዝጋት የራሱ ሆነ ትምህርት ቤት ለመክፈት ባለው ሕልም በዌብ ሳይቱና ከኅዳር 16-30 ቀን 2008 ዓ.ም. ባሳተመው ‹‹ስምዐ ጽድቅ ዘኦርቶዶክስ›› በተባለው ጋዜጣው 23ኛው ዓመት ቁጥር 5/ቅፅ 23 ቁጥር 333 ላይ የሦስቱም መንፈሳዊ ኮሌጆች መምህራንና ደቀ መዛሙርት ስም በጅምላ በሕፀፀ ሃይማኖት ስም ማጥፋቱ ነው ።

ሁሉም እንደሚገነዘበው በየትኛውም ቦታ በየትኛውም ጊዜ በማኅበረ ቅዱሳን ውስጥም ጭምር የሃይማኖት ሕፀፅ ያለበት ግለሰብ ሊኖር እንደሚችል መገመቱ አያዳግትም፤ ሆኖም እንደዚህ ያለ ሁኔታ ሲኖርና ተጨባጭ ማስረጃ ሲገኝ በሰከነ መንፈስ ለቅርብ ተጠሪው ውሳኔ ሰጭ አካል ማቅረብ በዚያም መፍትሔ ካልተሰጠ ደረጃውን ጠብቆ እስከቅዱስ ሲኖዶስ ድረስ በማቅረብ በቀኖናው መሠረት መፈጸም ሲቻል ቤተ ክርስቲያናችን አሉኝ በምትላቸው ዕውቅ ሊቃውንት የምታስተምርባቸውን፣ በሊቃነ ጳጳሳት ተመርጠውና ተመልምለው የተላኩት ደቀ መዛሙርት የሚማሩባቸውን፣ በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት



☎ 251-111-111989, 251-111-550577, 251-111-565747, 251-111-551013
Fax:- 251-111-552211
✉ 1283 አዲስ አበባ Addis Ababa
E-mail: abamatthiaspatriarch@yahoo.com
abagerima@yahoo.com

አባ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣

ABBA MATTHIAS I
Patriarch of Ethiopia, Archbishop of Axum,
Echegue of the See of St. Tekle Haimanot

ቁጥር
Ref. No

ቀን
Date ዓ.ም

የሚመሩ የአስተዳደር ኃላፊዎችና ሠራተኞች ያላቸውን ከፍተኛ የትምህርት ተቀዋማት በአጠቃላይ ሕፀፀ ሃይማኖት አሏቸው ብሎ በጅምላ መፈረጅ የሚጓጓለትን ልዩ ድብቅ ዓላማ ለመፈጸም አስቦ ካልሆነ በቀር በምንም ዓይነት መመዘኛ ትክክል ሊሆን አይችልም ።

ማኅበሩ በሚከተለው አካሄድ ማለትም በሚድያና በጋዜጣ ስም በማጥፋት ብቻ የሃይማኖት ሕፀፅ ያለባቸው ሰዎችን መከላከል አይቻልም፤ ይልቁንም ከላይ በተገለፀው ቀኖናዊ ሥርዓት በስም ጠቅሶና በማስረጃ አስደግፎ ለውሳኔ ሰጪው አካል በማቅረብ በቀኖናው መሠረት ውሳኔ ሲያገኝ ሕፀፀ ሃይማኖቱን በአግባቡ ማስወገድ ይችላል ። ማኅበሩ በቂ መረጃ ካለው ይህንን ቀኖናዊ፣ ሕጋዊና ትክክለኛ አካሄድ የማይከተልበት ሁኔታ ምን እንደሆነ ግልጽ ነው ። ‹‹የገበያ ግር ግር …›› እንደሚባለው ጉዳዩ ሳይጣራ በግርግር የቤተ ክርስቲያናችንን ት/ቤቶች ስም በማጥፋት ያልተፈቀደውና በሆቴል ውስጥ ተመርቆ የተከፈተው ዕውቅና የለሽ የራሱ ት/ቤትን ለማስፋፋት ጥሩ ዘዴ መስሎ ስለታየው ይመስላል ከማለት ውጭ ሌላ ምክንያት ሊኖረው አይችልም ።

ስለሆነም ይህን እውነት በመገንዘብ የሦስቱም ኮሌጆች ኃላፊዎች፣ ሠራተኞች፣ መምህራንና ደቀመዛሙርት ጥር 3 ቀን 2008 ዓ.ም. ያቀረባችሁት የተቃውሞ መግለጫ ለሚመለከተው አካል ቀርቦ ውሳኔ የሚያገኝ ይሆናል ።

ይሁንና አሁን እየተከሰተ ያለው ሁኔታ የመኖርና ያለመኖር ጥያቄ ስለሆነ የኮሌጆቹን ቀጣይ ህልውና በዘላቂነት ለመጠበቅ የተጠናከረ የተደራጀና ቀጣይነት ያለው ሥራ በመሥራት ማኅበሩ በቤተ ክርስቲያንና በት/ቤቶቿ ላይ የቀሠራቸውን የጥፋት ጣቶቹን መልሶ ወደኪሱ እስኪከትና ለቤተ ክርስቲያን ሉዓላዊ ሕግ ተገዥ እስኪሆን ድረስ የማያቋርጥ ትግል በማድረግ በንቃት መከታተል ይጠበቅባችኋል።



☎ 251-111-111989, 251-111-550577, 251-111-565747, 251-111-551013
Fax:- 251-111-552211
✉ 1283 አዲስ አበባ Addis Ababa
E-mail: abamatthiaspatriarch@yahoo.com
abagerima@yahoo.com

አባ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣
ሊቀ ጳጳስ ዘአኵስም፣
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣

ABBA MATTHIAS I
Patriarch of Ethiopia, Archbishop of Axum,
Echegue of the See of St. Tekle Haimanot

ቁጥር
Ref. No

ቀን ዓ.ም
Date

ስለሆነም ትምህርታችሁን፣ አንድነታችሁን፣ ሃይማኖታችሁንና ሰላማችሁን ከማስጠበቅ ጋር የቤተ ክርስቲያንን አንድነት፣ ሉዓላዊ ክብርና ህልውና ለማስጠበቅ በምታደርጉት እንቅስቃሴ ሁሉ ምን ጊዜም ቤተ ክርስቲያን ከጎናችሁ መሆኗን በዚህ አጋጣሚ ልናረጋግጥላችሁ እንወዳለን ።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ

ግልባጭ

- ለቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት
- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት
- ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት
- ለትምህርትና ማሠልጠኛ መምሪያ
- በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ለፌዴል ጉዳዮች ሚኒስቴር ጽ/ቤት
- ለሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
- በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ለፍትሕ ሚኒስቴር ጽ/ቤት
- በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን
- ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት

  አዲስ አበባ
- ለትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርእሰ መስተዳድር ጽ/ቤት
- ለትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፖሊስ ኮሚሽን
- ለትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ ጽ/ቤት

  መቐሌ
- በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የሚገኙ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ለሚመሩት አህጉረ ስብከት

  በያሉበት



☎ 251-111-[illegible] 251-111-550577
251-111-[illegible] 251-111-551013
Fax:- 251-111-552211
1283 አዲስ አበባ Addis Ababa
E-mail: abamatthiaspatriarch@yahoo.com
abagerima@yahoo.com